የዶ/ር ነገደ ጎበዜ አዲስ መጽሐፍ

"…ይህንን የትግሉን ህዝባዊ ገፅታ ችላ ብለን እነዚህን ሚሊዮኖች የሚያካትት ህዝባዊ የትግል ማእበል ለመቀስቀስ፣ መቀስቀስ ብቻ ሳይሆን ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችለን የጋራ ስትራቴጂ አውጥተን ካልተንቀሳቀስን በስተቀር "በእኛና በእነሱ" መሃከል በተወሰነ የትግል ክፈፍ ከብረት ድስትና ከሸክላ ድስት ፍልሚያ፤ ሸክላ በአሸናፊነት ይወጣል በሚል የአጉል ህልም ዓለም ውስጥ ነን ማለት ይሆናል፡፡" ዶ/ር ነገደ ጎበዜ

በምርጫ 97 ወቅት አቶ መለስ ዜናዊ በፓርላማቸው ውስጥ ተቃዋሚዎችን ለመወንጀል እየተንጨረጨሩ ያነሱት ስም ነገደ ጎበዜ የሚለውን ነበር። ያ ስም እንደገና ተመልሶ መጥቷል። አሁንም ከመጽሐፍ ጋር ነው የመጣው። ዶ/ር ነገደ ጎበዜ "ይድረስ ከየካቲት ለግንቦት"የሚል አዲስ መጽሐፍ ይዘው መጥተዋል።

ቀደም ሲል "ሕገ መንግሥት ምርጫና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ (ከትላንት ወዲያ እስከ ነገ)" የሚል አነጋጋሪ መጽሐፍ ያሳተሙትና የመኢሶን ከፍተኛ አመራር አባል የነበሩት ዶ/ር ነገደ ጎበዜ በዚህኛው መጽሐፋቸው ብዙ የደከሙ መሆናቸው ያስታውቃል። አሁን ያለንበትን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ ለመመልከት እስከዛሬ ከነበረው መመሳሰልና መለያየቱን መርምረዋል። በጊዜ ሂደት ውስጥ አሁንም ያልተውናቸው ያልተማርንባቸው ዛሬም ትናንትም የምንደጋግማቸው ቋሚ ስህተቶቻችን ምን እንደሆኑ አይተው ለማሳየት ሞክረዋል።

ከቅድመ አብዮት ጀምረው አሁን እስካለንበት ድረስ ብዙ ነገሮችን በጥልቀት ተመልከተዋል። እስከታህሳስ የነበሩ የለውጥ ሙከራዎችን፣ በዘመኑ የነበሩ የሥልጣኔ ኃይሎችን፣ የባዕዳንን ደባና ወረራ፣ የለውጥ ማቆጥቆጥ፣ የለውጥ ኃይሎች መከፋፈልና መዳከም፣ ስለታህሳስና ታህሳሳውያን፣ ስለመፈንቅለ መንግስቱ ሙከራ ሁሉ ፈትሸዋል። እስከ የካቲት ዋዜማና ማለዳ ድረስ ያለውን ከዚያም ወዲህ በየደረጃው ያለውን ተመልክተው በለውጡ የተገኙ ድሎች ወዲያው የተቀለበሱባቸውንም መንገዶች አዋዝተው ለመተንተን ሞክረዋል። "የደርግ ቀኝ ኋላ ዙር አካሄድና ስለተራማጁ ሠፈር ክፍፍልም" ጽፈዋል። ህዝባዊ ሥልጣን እንዲመነጭባቸው ታስበው ስለተዘረጉ ተቋማት፣ ስለ የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤትና የገበሬ ማህበራት እንዲሁም ስለ ደርግ አንጃዎች ፍልሚያና ነጭ ሽብር ብዙ ነገሮችን በዝርዝር እያነሱ በመጽሐፋቸው ተንትነዋል። የአብዮቱም ሆነ የተራማጅ ኃይሎች እንቅስቃሴ ስለተቀለበሰበት ሁኔታም "1969 የቅልበሳው ዘር ሲዘራ" 1970 ቅልበሳ በሽብር" የቀይሽብር ዓላማና ኢላማ በሚል በሚል ርዕስ ሥር ትንታኔያቸውን ሰጥተዋል። እንደሳቸው ገለጻ ብዙ ሰው በከተማ ስለተደረገው ፍጅት ብቻ ነው የሚያወራው። እንዲያውም በከተማ ካለቀው በገጠር የተፈጀው አርሶ አደር እጅግ ብዙ ነው። ደርግ አርሶ አደሩን ስለፈጀበት ምክንያት ፀረ ገበሬ ፖሊሲዎችና ያስከተሉት ምስቅልቅል፣ ሽብር በገጠር - ምክንያቱና ስፋቱ በሚል ርዕስ በሰፊው ጽፈዋል። ይህ ሁሉ የየካቲት ቅልበሳ ዘርፈ ብዙ መልኮቹ ሲሆን አገር ከዚያ የጀመረ እሳካሁን ከቀውሶች አዙሪት አልወጣም። ድሎች ተቀልብሰው ጽልመትና ጨለምተኝነት እየነገሱ መምጣታቸውን አሁን ከምርጫ 97 በኋላ ከሆነው ጋር እያነጻጸሩ ይፈትሻሉ። በዚያ ላይ እንደረሀብ የመሬት ስሪትና ስለ ዴምክራሲው መጥፋት ስለ አጥፊ ፖሊሲዎች ቀጣይነትና መዘዛቸው የመሳሰሉ ተያያዥ ችግሮችን በየርስዓቸው ያነሳሉ።

የገጠሩን ልማት ግንጥል ስትራቴጂ ስለ ኢንደስትሪ መስፋፋት በደርግ ጊዜ ስለነበሩ የመንግስት እርሻና ሠፈራዎች እያነሱ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በኢኮኖሚው ላይ ሊኖረው ስላለው ተችግር ይተቻሉ። ወዲህ ወዳለንበት ዘመንም ተያያዥና ተወራራሽ ነገሮችን እያመጡ ኢህአዴግ በግንቦት 97 ምርጫ በገጠርም በከተማም በዝረራ ከተሸነፈ በኋላ የተከሰተውን

ዙሪያ ገጠም ቀውስ ይገመግማሉ። “አንዳንድ ዜጎች በየካቲት ቅልበሳ ማግስት አገራችን ከገባችበት አንድነቷንና ህልውናዋን ሳይቀር ፈተና ውስጥ ካስገባው ቀውስ ጋር ያነፃፅሩታል፡፡” ያሉት አቶ ነገደ “ እውነታቸውን ነው፡፡” ባይ ናቸው።

ሁለቱንም ቅልበሳዎች “የኖርኩ” እንደ መሆኔ መጠን ከዚህ ንፅፅር ጠለቅ ብዬ ለመሄድ ሞከርኩ፡፡ ከዚህም በመነሳት የየካቲት ድሎች ምን ነበሩ? እንዴትስ ተገኙ? እንዴት ተነጠቁ? የዚህ ሽንፈት የአጭርና ረዥም ጊዜ መዘዞች ምንድን ነበሩ? ያኔ ቅልበሳውን ለመመከት ለምን አልተቻለም? በዚህ ሁሉ የዓለም አቀፉ ኮሚዩኒቲ ሚና ምን ነበር? ዛሬ ከዚህ ሁሉ የምንማረው ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች በአእምሮዬ ተመላለሱ፡፡” ይላሉ ነገደ ጎበዜ።

በወቅቱ በሃገር ቤት በህቡእ ይሰራጭ ለነበረው ለመኢሶን ልሳን ለ“ሰፊው ህዝብ ድምፅ” ከውጭ ሆኜ እልካቸው የነበሩትን ትንተናዎች፤ ለአመራሩና ለሌሎች ጓዶች የፃፍኳቸውን ማስታወሻዎች፤ ስለ አብዮቱ ሽንፈት፤ ስለ ቀይ ሽብርና የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ፡ ስለ ስመ ጥፉው “የክፍለ ዘመኑ ረሀብ” ወዘተ.... በባእዳን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶቸች (መያዶች) ስብሰባዎችና የትምህርት ተቋማት እየተገኘሁ የሰጠኋቸውን ገለጣዎችና ያቀረብኳቸውን ራፖሮች ለሰላሳም ይሁን ሰላሳ አምስትም ዓመታት ወደኋላ እየተመለስኩ ማንበብ ጀመርኩ፡፡” በማለት ያነበቡትን ጽፈዋል። የጻፉት ግን የሆነውን ብቻ አይደለም። ለምን እንደሆነ ጠይቀዋል። የጠየቁትም ለትችትና ዳኝነት አይደለም። ይልቁንም መፍትሄ ለማመንጨት ይመስላል። መጽሐፋቸው ምን እንደሚያደርግ በመግቢያቸው ላይ ይህን ጽፈዋል፡-

“ከክፍለ ዘመኑ ማለዳ ጀምሮ በፖለቲካው መድረክ ብቅ ያሉት አዳዲስ የለውጥ ኃይሎች ለዚች አገር “ስልጣኔን”፣ ለህዝባችንም ሰላምን፡ መሻሻልን፡ ፍትህን ዴሞክራሲን ይጠይቁ እንደ ነበረ ሁሉ አለመታደል ሆኖ ዛሬም ከመቶ ዓመታት በኋላ እነዚህኑ ጥያቄዎች አንግበን ለመዋደቅ የተገደድንበት ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን፡፡ በመሃል ለህዝባችን ገና እውን ላልሆኑት ለእነዚህ መሰረታዊ እሴቶች እውንነት ከፍተኛ መስዋእትነት የተከፈለባቸው ተጋድሎዎች ቢደረጉም ፍሬ ያልሰጡበት ዋና ዋና ምክንያቶች በዚህ መጽሃፍ ውስጥ በሰፊው ይተነተናሉ፡፡”

አሁን ያለውም ሁኔታ አደገኛ መሆኑንንም ሲገልጹ “በሃገር ውስጥ ደረጃ ዛሬ በስልጣን ላይ ያለው ቡድን ህዝባችንን በብሄር፣ በጎጥና በሃይማኖት የመከፋፈሉን ፖሊሲ በመንግስት በጀት የሚያራምድ፣ በአንድ ወቅት አቶ ስብሃት ነጋ በይፋ እንደተናገሩት ለኤርትራ መገንጠል “ከሻዕቢያ ይበልጥ የተዋደቀ” በሌላ በኩል ደግሞ “እኔ ከስልጣን ከተወገድሁ ሃገሪቱን እበታትናታለሁ” እያለ ነጋ ጠባ የሚዝት “አስገንጣይ ተገንጣይ” ሊባል የሚችል ቡድን ነው፡፡ ለዚህ የጥፋት ዓላማው ደግሞ ጠንካራ የሆነ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የጦር፣ የፖሊስ የፀጥታ ኃይል፣ የዳበረ የገንዘብና የማቴርያል አቅም አለው፡፡ በሃገራችን ህልውና ጉዳይ ዛሬ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ከቀድሞት ሙከራዎች በተፃራሪ በአንድ በኩል ፀረ አንድነት ኃይሎች የመንግስት ስልጣን የጨበጡበት በሌላ በኩል ደግሞ  የዴሞክራሲያዊ አንድነት ኃይሎች ከነድክመታቸውና ክፍፍላቸው በተቃዋሚነት ተሰልፈው የሚገኙበት አስገራሚና ከዚህ በፊት በሃገራችን ታይቶ የማይታወቅ አደገኛ ሁኔታ ነው፡፡ “

ዶ/ር ነገደ በስትራቴጂክ ስልቶች ስለ ዘረዘሯቸ የመፍትሄ ሀሳቦች ሲገልጹ ወግ ባለው ውጤታማ ሊያደርግ በሚያስችል መልኩ ስለመደራጀትም ይመክራሉ። ተዝረክርኮ በመቀመጥ ለውጥን መጠባበቅ የማይሆን መሆኑን የየካቲቱን ለውጥ አብዮት በምሳሌነት ያነሳሉ። አብዮቱ የተቀለበሰው ብዙዎቹ እንደሚሉት አብዮቱ ራሱ በግብታዊነት ስለመጣ አይደለም። በመጽሀፋቸው እንደዚህ ብለዋል-

“የየካቲት አብዮት ግብታዊ ነበር ሲባል የረዥም ጊዜ የትግል ልምድ አካብቶ ይህንን ህዝባዊ ማእበል ከመሃል ሆኖ የቀሰቀሰና የመራ አንድ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የድርጅቶች ስብስብ አልነበረም ለማለት እስከሆነ ድረስ ይህ አባባል ትክክል ነበር፡፡ ግን ደግሞ ሁኔታውን ጠለቅ አድርገን ስንመለከት በተለይ ሁሉም ብሶቱን አንግቦ እንዲነሳ የተደረገውና በጎ የህዝባዊ ትግል ማእበል እመርታ ለመቀስቀስ ወሳኝ የሆነ ሚና የተጫወተው ሂደት አመራር አልባ አልነበረም፡፡

ዶ/ር ነገደ እንዲያውም በወቅቱ የነበረው የመደራጀት ፍላጎትና ግንዛቤ የቱን ያህል እንደነበረ ሲገልጹ

“የተካሄደው ትግል በተንቀሳቀሱት የህብረሰብ ክፍሎች በሙሉ የነዚህን ክፍሎች ችግሮችና ብሶቶች የሚካፈሉ “ውስጥ አዋቂዎች” የመደራጀት ወረርሽኝ ሊባል በሚችል አካሄድ እንደሁኔታው በይፋም ሆነ በህቡእ በየፊናቸው እየተደራጁ የቀሰቀሱትና ያካሄዱት ዘርፈ ብዙ ትግል ነበር፡፡ ዛሬ በዚህ መልክ ተደራጅቶ መታገል ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ነው ብዬ ስለማስብ ስለነዚህ “የህዝባዊ ትግል እመርታ አንቀሳቃሽ ኃይሎች” ብዬ ስለምጠራቸው ዜጎች ማንነትና ሊጫወቱ ስለሚችሉት ሚና፣ ከዚያም አልፎ በሃገር ውስጥ በይፋም ሆነ በህቡእ ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ወገኖችና ዲያስፖራው ይህንን በጎ እመርታ ለመቀስቀስ ሊያደርጉ ስለሚችሉት አስተዋጽኦ ያለኝን ሃሳብ በሰፊው ለማቅረብ እሞክራለሁ፡፡ “ ብለዋል። በመጨረሻም እንዲህ የሚል ነገር በመጽሐፋቸው ውስጥ ተጠቅሷል፦

ቀጣዩን ትግል በተመለከተ በዚህ መጽሃፍ ውስጥ የማቀርባቸው ሃሳቦች በዓለም ከአሉ ቀውሶችና ችግሮች ሁሉ ከተገቢ ድርሻዋ በላይ ለተሸከመችው ለዚች መከረኛ አገራችን ውስብስብ ችግሮች ያለው አንድ መፍትሄ “ይኸ ነው” በሚል መንፈስ የተወረወሩ አይደሉም፡፡ ከአንድ ከአስር ዓመት በፊት በአንድ ቃለ ምልልስ ላይ “ለዚች አገር ችግሮች ቀላል መፊትሄ የለም፡፡ ቢኖር እስከ ዛሬ ይሰማ ነበር፡፡” ብዬ ነበር፡፡ ዛሬም ከዚህ የተለየ አቋም ሊኖረኝ አይችልም፡፡ ቀላል መፍትሄ የለም ሲባል ግን መውጫ የሌለው ሁኔታ ውስጥ ነን ማለት አይደለም፡፡ ከእስካሁኑ የኪሳራ ሂደት ትምህርት ቀስመን ወደፊት ለመራመድ የሰከነና ህዝቡንና ሃገርን የሚያስቀድም ውይይት አካሂደን ግልፅ የሆነ ሀገር አድን ስትራቴጂ ለመንደፍ እንችላለን፡፡ የሚሰነዘሩት ሃሳቦች እንዲህ አይነቱን ውይይት ለመቀስቀስ ከቻሉና ይህ ውይይት ግልፅ በሆነ የጋራ ትግል ስትራቴጂ ከተቋጨ ይህ መጽሃፍ ግቡን መቷል ማለት እችላለሁ፡፡

ዶ/ር ነገደ በመጽሐፋቸው የሰነዘሯቸው የመፍትሄ ሀሳቦች ምንድናቸው? ይህን መጽሐፉ ራሱ ቢመልሰው የተሻለ ይመስለናል።

(መጽሓፉን ለማግኘት በስልክ 1-408-605-3988 ይደውሉ)